የ ኢ ት ዮ ጵ ያ ብ ሔ ራ ዊ ባ ን ክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
ADDIS ABABA

# አዲስ የታተሙ የኢትዮጵያ የብር ኖቶችን ሥራ ላይ ለማዋል የወጣ መመሪያ ቁጥር ከማዳ/2/2013

በዝውውር ላይ የሚገኙ ሕጋዊ የገንዘብ ኖቶች በሥራ ላይ ከዋሉ ረጅም ጊዜ የተቆጠረ ስለሆነ ለሐሰተኛ የገንዘብ ኖቶች ሕትመት እና ስርጭት እየተጋለጡ በመሆኑ፣

የተሻሻሉ የደህንነት መጠበቂያ ምልክቶችን በኖቶቹ ላይ በማድረግ የአገሪቱ ሕጋዊ የገንዘብ ኖቶችን የጥራት ደረጃ በማሻሻል የሀሰተኛ ገንዘብ ሕትመት እና ስርጭት ወንጀልን መከላከል በማስፈለጉ፣

ሕብረተሰቡ ለትላልቅ የገንዘብ ኖቶች ያለውን ፍላጎት ከግንዛቤ ዉስጥ በማስገባት የባለ 200 ብር ኖት በማሳተም እና የገንዘብ አቅርቦትን በማሻሻል የህብረተሰቡን ፍላጎት ማርካት አስፈላጊ በመሆኑ፣

ከባለ 5 ብር በስተቀር በአሁኑ ጊዜ በዝውውር ላይ የሚገኙ የገንዘብ ኖቶችን ባንኩ በሚያሳትማቸው አዳዲስ የገንዘብ ኖቶች ሙሉ በሙሉ በመቀየር የገንዘብ አጠቃቀምን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ (እንደተሻሻለ) አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 5(1)፣ 18(2) እና 27 (2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "አዲስ የታተሙ የኢትዮጵያ የብር ኖቶችን ሥራ ላይ ለማዋል የወጣ መመሪያ ቁጥር ከማዳ/2/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።



አድራሻ፡ ሱዳን ጎዳና ፖ.ሣ.ቁ. 5550/2048 ፋክስ [illegible] 45 88 ስልክ ቁጥር 0115 51 74 30 አ.አ
ADDRESS: SUDAN STRCET P.O.BOX 5550/2048 FAX No. 0115 51 45 88 TEL. No. 0115 51 74 30 ADDIS ABABA
TELEGRAPHIC ADDRESS: N A T I O N B A N K
CODES-USED PETERSON 3rd & 4th ED BENTLEY'S 2nd PHRASE A.B.C. 6th EDITIO
E-mail: nbe.excd@ ethionet.et Website. www.http:// www.nbe.gov.et

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ፦

2.1 "ባንክ" ማለት የባንክ ሥራ እንዲያከናዉን በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠዉ ኩባንያ ወይም የመንግሥት ባንክ ማለት ነዉ፤

2.2 "መደበኛ ግብይት" ማለት ሕጋዊ በሆነ የሥራ ፈቃድ በቀን ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ ብር) በላይ የሚደረግ ግብይት ነዉ፤

2.3 "ሕጋዊ የብር ኖቶች" ማለት የኢትዮጵያ ባለ 200 ብር፣ ባለ 100 ብር፣ ባለ 50 ብር፣ ባለ10 ብር እና ባለ 5 ብር ኖቶች ናቸው፤

2.4 "ብሔራዊ ባንክ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፤

2.5 "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

2.6 "አዋጅ ማለት" የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ /እንደተሻሻለ/ አዋጅ ቁጥር 591/2000 ነዉ፤

2.7 ማንኛዉም በወንድ ጾታ የተገለፀ የሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. የብር ኖቶች ለውጥና የኖቶቹ ዋጋ

በዝውውር ላይ ያሉት የብር ኖቶች የገንዘብ ለውጥ ይፋ ከሚደረግበት ቀን ጀምሮ ታትመው በሚሰራጩ አዳዲስ የብር ኖቶች በቀጥታ የሚለወጡ ሲሆን አዲሶቹ የብር ኖቶች ቀደም ሲል በዝውውር ላይ ከነበሩት የብር ኖቶች ጋር እኩል አንድ ብር ለአንድ ብር ይለወጣሉ።

## 4. የመመሪያው አፈጻጸም

ይህ መመሪያ ከመጽናቱ አስቀድሞም ሆነ የኖቶቹ ለውጥ እንዲደረግ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ በማናቸውም ሕግ፣ ስምምነት፣ ሽያጭ፣ የሐዋላ ክፍያ፣ የገንዘብ መክፈያ ወረቀት፣ የገንዘብ ሰነድና ዋስትና እንዲሁም በማናቸውም ገንዘብ ነክ በሆኑ ጉዳዮች የተመለከተው የገንዘብ መጠን ባንኩ ወደፊት ይፋ ከሚያደርግበት ቀን በፊት የወጣ አንድ ብር አዲስ በወጣው አንድ ብር ሒሳብ ይለወጣል፡፡

## 5. የቀድሞ የብር ኖቶች ሕጋዊነት ስለሚቆይበት ጊዜ

ብሔራዊ ባንክ ወደፊት ይፋ ከሚያደርግበት ቀን ጀምሮ በዘጠና (90) ቀናት ውስጥ ያልተለወጡ የብር ኖቶች ፈጽሞ የማይተኩና ለማናቸውም ክፍያ የማያገለግሉ ይሆናሉ።

## 6. የብር ኖቶቹ የመለወጫ ስፍራዎች እና አፈጻጸም

6.1 በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ሥር በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ባንኮች በሙሉ የኖቶች ለውጥ አገልግሎት ይሰጣሉ።

6.2 የገንዘብ ኖቶች ለውጥ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ባንኮች የጥሬ ገንዘብ ክፍያ የሚፈጽሙት በአዳዲሶቹ የብር ኖቶች ብቻ ይሆናል።

6.3 ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው ዝርዝር መሠረት ከባንኮች የኢሹ ቅርንጫፎች በተጨማሪ ጊዜያዊ የገንዘብ ኖቶች መለወጫ ጣቢያዎችን ከፍቶ አገልግሎት እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል።

6.4 ከብር 5,000 (አምስት ሺ ብር) በላይ ገንዘብ የሚለወጠዉ በደንበኛዉ ስም በተከፈተ የተቀማጭ ሂሳብ በኩል ብቻ ይሆናል፡፡

6.5 አንድ ሰዉ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 6.4 መሠረት የገንዘብ ለዉጥ አገልግሎት የሚያገኘዉ የራሱን ሂሳብ በመጠቀም ብቻ ይሆናል፡፡

6.6 ከመደበኛ ግብይት ዉጭ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ ብር) በላይ ገንዘብ በእጁ የያዘ ማንኛዉም ሰዉ በኢሹ ቅርንጫፍ የአዲሱ የገንዘብ ኖት ለዉጥ ሥራ በተጀመረ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ሕጋዊ ገደቡን ጠብቆ የያዘዉን ገንዘብ መለወጥ ይኖርበታል፡፡

6.7 የገንዘብ ለውጥ ስለሚፈፀምበት፣ ጊዜያዊ የመለወጫ ጣቢያዎች ስለሚከፈቱበት እና ስለሚዘጉበት ሁኔታ ብሔራዊ ባንክ በ"ጋይድላይንስ" ሊወስን ይችላል።

6.8 መደበኛ ግብይት በማያከናዉን ሰዉ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ ብር) በላይ ስለሚደረግ የገንዘብ ለዉጥ ብሔራዊ ባንክ በሚጠይቀዉ መሠረት ባንኮች ለብሔራዊ ባንክ በየሣምንቱ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

6.9 ማናቸዉም የመኪና፣ የቤትና የከበሩ ማዕድናት እንዲሁም ሌሎች የግብይት መጠናቸዉ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር) በላይ የሆኑ መደበኛ ግብይቶች በባንኮች በኩል ብቻ መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

6.10 በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር CMD/1/2020 እና አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀፅ 26(1)(መ) መሠረት ከመደበኛ ግብይት ዉጭ ከብር 1.5 ሚሊዮን (አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር) በላይ ገንዘብ በእጁ ይዞ የተገኘ ሰዉ ገንዘቡ ይወረሳል፡፡

## 7. የኖቶቹ ዓይነት

7.1 አዲስ የወጡት የብር ኖቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ባለ 200 ብር ኖት፣
- ባለ 100 ብር ኖት፣
- ባለ 50 ብር ኖት፣ እና
- ባለ 10 ብር ኖት፡፡

7.2 አሁን በዝውውር ላይ ያለው ባለ 5 ብር ኖት የአገሪቷ ሕጋዊ የገንዘብ ኖት ሆኖ ይቀጥላል፡፡

7.3 ዓይነታቸዉ፣ ቀለማቸዉና ምልክታቸዉ በባንኮችና በተለያዩ ቦታዎች በሚለጠፉ ማስታወቂያዎችና በመገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ የሚገለፁት አዲሶቹ የገንዘብ ኖቶች የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕጋዊ የገንዘብ ኖቶች ይሆናሉ፡፡

## 8. የመተባበር ግዴታ እና ኃላፊነት

ማናቸውም ሰው ይህንን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የመተባበር ግዴታ እና ኃላፊነት አለበት። .

## 9. የመመሪያው ገደብ

የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች አሁን በዝዉዉር ላይ ባሉት ቅንስናሽ ሳንቲሞች እና በባለ 5 ብር ኖት ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸዉም።

## 10. ቅጣት

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛዉም ሰዉ በአዋጁ አንቀጽ 26(1)(መ)፣ 26(2)(ሀ) ወይም 26(2)(ለ) ወይም አግባብ ባለዉ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል፡፡

## 11. መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከመስከረም 5 ቀን 2013 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ይናገር ደሴ (ዶ/ር)
ገዥ

BANK OF ETHIOPIA